አማኑኤል አለማየሁ (ደጀና)02-07-18

# ጥልቅ ተሓድሶ ለምን?

በአገራችን ፖለቲካ በተለይም አሁን ባለንበት ወቅት ኢህአዴግ ወደ ጥልቅ ተሃድሶ ገብቼ ይህንና ያንን አየሁ ገመገምኩ ሲል እስማለሁ እና ለምን ብየ እጠይቃለሁ፡፡ ህወሓትስ ጥልቅ ተሃድሶ ያድርግ ሌሎች አባል ድርጅቶች ግን ለምን ጥልቅ ተሃድሶ ያደርጋሉ ምን ይጠቅማቸዋል?

ባለፉት 27 ዓመታት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የመጣው ለውጥ (ከተለመደው ጋር በማነፃፀር) ቀላል የማይባል ነው፡፡ በተለይም ቋንቋ እያለህ ቋንቋህን በት/ቤት፣ ፍርድ ቤት፣ ጤና ጣቢያ፣ ባጠቃላይ የመንግስትና የግል ተቋማት እደዚሁም በፅሁፍ፣ በሚዲያ በተለይ በአካባቢህ ጉዳዮ እንዳትጠቀምና አንድ አሃዳዊ ቋንቋ እና ባህል መፍጠር ይቻላል በሚል አገርን ከብዝሃ ብሄር ብሄረሰብ አቀፍ አገርነት (multi-national state) ወደ አንድ በሄር አቀፍ አገርነት (nation state) መቀየር ይቻላል የሚል በቅኝ ገዥዎች ተሞክሮ ብዙም ያልተገፉበትን አስተሳሰብ በመቀየርና ሁሉም ብሄርና ብሄረሰቦች በኢትዮጵያ እጣፋንታ ይመለከታቸዋ ለሚለው አስተሳሰብ እንደ ፖለቲካዊ ድርጅት ህውሓት ትልቅ ሚና ነበረው፡፡

በመሆኑም የነበረውን የስርዓት ለውጥ መሪ ሚና መሰረት ተደርጎ ተወቃሽ/ተመስጋኝ ለማድረግ መሞከሩ ብዙም ከእውነታ የራቀ አይደለም፡፡

አሁን አሁን እየበዛና ላለፉት 27 ዓመታት በጥቂት ቃላቀባዮችና በህውሓት/ኢህአዴግ ተፃራሪ ከተሰለፉቱ ብቻ እንሰማው የነበረውን ጠበብ ያለ ወቀሳ አሁን አድማሱን አስፍቶ በዛ ባለ የማህበረሰብ ክፍልና የኢህአዴግ አባል ድርጅት በሆኑት አመራር አካላትና ተከታይ አባሎቻቸው ሳይቀር እንደ ጥዋት ማታ ፀሎት እየሰማን መዋል ማደሩን አስተሳሰቡን የማንጋራ ሰዎችም እየለመድነው ስንሄድ አስተሳሰቡን የሚጋሩት እየጣማቸው ሄዶ እውነት ነው ብለው እስከ ለመስዋእትነት እየተሰለፉበት/እየተሰለፉለት ይገኛሉ፡፡

## እውን ህውሓት በሁሉም ቦታ የበላይ ነው?

አሁን ባለቸው ኢትዮጺያ እያንዳንዱ ክልል አስተዳዳሪ ድርጅት አለው፡፡ ህውሓትም ልክ እንደሌሎቹ የራሱ ክልል አለው የትግራይ ክልል፡፡ በትግራይ ክልል ለተፈፀሙት ሃጢያቶች በከፊል ሳይሆን መቶ በመቶ ተጠያቂው ህውሓትና የበሰበሱት መሪዎቹ ተጠያቂዎች ናቸው፡፡ በትግራይ ህዝብ ልጆች የትምህርት፣የጤና፣የኢኮኖሚ እድገት ጥፋቶች ላይ የፈፀሙት ግፍ በተለይም ህዝቡ በስጋትና በፍርሃት እንዲኖር የተጫወቱት የስነልቦና ጦርነት ከህውሓት መሪዎች ተከታዮቻቸው ውጭ ማንም ተጠያቂ ሊኖር አይችልም፡፡ ህዝቡ በትእግስት እና በማስተዋል አካባቢውን አፈር ለብሶ አፈር ምሶ ለማልማት ከመሞከር በላይ ድንቁርናቸውንና ጥጋባቸውን መሸከም ያቃታቸው እምቦቀቅላ ህፃን በሚመስሉ በሚሊዮኖች በተገዙ ጃፓን ሰራሽ መኪኖች አቧራ እያቦነኑበት ሲያልፉ እንኳን ሰብስበው የሚነግሩትን ቃላቸውን እንጅ በሙስና የተጨማለቀ ውሉዋቸውን ቅድሚያ ሰጥቶ ካልጠፉችሁ፣ ካሞታችሁ አላላቸውም፡፡ ስለሆነም ጥጋባቸው ጥግ ደርሶ እንደ ድሮው የሮማን ጳጳሳት በወሳንሳ እንዲሸከማቸው ቢፈልጉም አይገርመኝም፡፡

ስለዚህ ህውሓት በትግራይ በተፈፀመው/ለፈፀመው ስህተት ጥልቅ ተሃድሶ ለማድረግ ሱባኤ ገብቶ አባላቱን ቢገመግም በርግጥ ይገባኛልበርግጥ ትክክል ነው፡፡ ባለፉት 27 ዓመታት የትግራይ ህዝብ ከህውሓት ጋር አብሮ እንዲወቀጥና ለዘረኛና በዘር ፖለቲካ ለተጠመዱት ብቻ ሳይሆን ዘረኛ ለመሆን በየቤታቸው እየተፈጠሩ ለመጡት ለወደፊቱም የዘረኝነት መፈልፈያ ለሆኑት አንዳንድ ተቋማት ማዳበርያ እየሰጠ ዘረኝነቱንና የትግራይ ህዝብ መጥላቱን እዲቀጥሉበት እየመገበ ሲያሳድጋቸው በመኖሩ መታደስ መገምግም እንዲሁም ሱባኤ መግባት ያስፈልገዋል፡፡ የህውሃት ልታደስ ማለት ከበቂ በላይ ብዙ ምክንቶች ስላሉት እቀበላዋለሁ ህውሓት ክልሉ እንዲታደስ እፀልይለታሁ፡፡

<u>ሌሎች የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችስመታደስ አለባቸው ወይስ እንደ አዲስ መፈጠር አለባቸው?</u>

ሌሎቹ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በተለይም ብአዴንና ኦህዲድ የሚያስተዳድሩትን ክልል በቅጡ የመምራት ሃላፊነት ልክ ህወሓት በጥፋቱ እንደሚጠየቅበት ሃላፊነት አለባቸው፡፡ ለማንኛውም ጥፋቱ በክልሉ ውስጥ ለሚፈፅሙት/ለሚፈፀመው በዜጎች በህዝብ ብሎም በአስተሳሰቦች ላይ ለሚደርሰው ጥቃት ተጠያቂዎች መሆን አለባቸው፡፡

አሁን ባለችው ኢትዮጲያ በፌዴራል ደረጃ የሚተዳደር ህዝብ ይሁን ግለሰብ/ ዜጋ የለም፡፡ በተመሳሳይ በፌዴራል ደረጃ የሚተዳደር ቅንጣት መሬት የለችም እንዳንዱ ዜጋ እና እንዳንዱቅንጣት መሬት አስተዳዳር የክልል መንግስት እና መንግስት የሆነ ፓርቲ አላት፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሳይቀሩ አስተዳዳሪ ክልል የቀበሌ መታወቂያ የሚሰጥና የሚነሳ ቀበሌ አላቸው (ስልጣኑ ቢኖረውም ሊፈራቸው እንደሚችል ታሳቢ አድርጌ) ስለሆነም በፌዴራል ቁጥጥር ስር ያለ ሰውና መሬት የለም፡፡

ፌዴራል መንግስት የተባለውም በቁጥር ከተለካ አብዛኛውን በስልጣንቢለካም ከሞላጉደል አብላጫውንየያዙት እነዚሁ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የሆኑቱ ከላይ የጠቀስኳው ሁለቱ ድርጅቶች ናቸው፡፡ አንዳንድ የፌዴራል መስሪያቤቶችና ተቋማት ትግርኛ ተናጋሪ አገልግሎት ፈላጊ ወይ ስልክ ተደውሎለት ወይንም እንደሱ ተገልጋይ ትግርኛ ተናጋ አግኝቶ በትግርኛ ሰላምታ ቢለዋወጥ ትግርኛ መናገር በአዋጅ ተከልክሏል የተባለ ይመስል ከሰራተኛ እስከ ደንበኛ የትግርኛ ተናጋሪዎች ላይ ማፍጠጥየተለመደ ነው፡፡ ከዚህም በዘለለ እሱ እኮ ትግሬ ነው አታስተናግዱት አይነት ወከባና ግልምጫ የሚብሰው ደግሞ ራሱን በእሽክርና እና በአዳሪነት ባስቀመጠ የህወሓት ወኪል ተብየ ባለስልጣን ላይ የከፋ ነው፡፡ አጋጣቢውን አግኝቶ ትግርኛ ተናጋሪ ተገልጋይ ከመጣለት ስለቱ እንደሰመረለት ፀሎተኛ ከፍ ባለ ድምፅና በኩራት ትግርኛ ተናጋሪውን ማሸማቀቅና አገልግሎት አለመስጠት እንደ ጀብድ እንዲያዝለት ያሳያል፡፡

ባለፉት 26-27 ዓመታት ለሁሉም ሃጢያት ህውሓት ሲወነጀል ነብሳቸውን ይማርና ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ይህ ህወሓትን ብሎም የትግራይ ህዝብን ውንጀላ ወደ ሚታየው የዘቀጠ የዘረኝነት ቋንቋእስኪቀየር ድረስ አባብለው ከቻሉም ጨምረውበት ተንከባክበው አሳድገውታል፡፡ ቀደም ብሎም በተለይም ከደርግውድቀት ማግስት የህውሓት አመራር ነበር አባላቱን በ1985 ዓ/ም ሰበስቦ ሲያወያይ ህውሓት ከወደቀ ታጋዮን ብሎም የትግራይን ህዝብ ዘረኛ ጠላቶቻችን በነቂስ ይበቀሉና ብሎ አስተምህሮት ሲሰጥ ነበር፡፡ ታድያ ይህን ያወቀው ህውሓት የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በሚያስተዳድሩትክልል ኮሽ ላለች ሁሉ፣ ለተዘረፈው መሬት፣ ለገቡበት ሃጢያት፣ ለፈፀሙት ወንጀል፣ በህልም ላዩት ቅዠት ሁሉ ተጠያቂ የትግራይ ወያኔ (ቃሉን ልብ በሉ የትግራይ ህዝብና ድርጅት ትርጓሜ በሚሰጥ መልሱ) ሲወነጅሉ ለምን ዝም አለ፡፡ እዚህ ላይ ሳስበው ሌቦችም፣ ሙሰኞችም

በድርጅቱት ደረጃ ህወሓትም የሚፈሩት የትግራን ህዝብ ይሆን እንዴ?ሳልሳይ ወያኔ ያሰነሳብናል ብለው ይሰጉ ይሆን እንዴ ብየ መልስ ሳላገኝ አሁንም እያሰብኩ ነው፡፡

ኦህዲድና ብአዴን በየክልላቸው የገበሬን መሬት ገበሬውን እያፈናቀሉ ሲቸበችቡና ከእያንዳንዱ ድሃ ተገልጋይ መቀነት እየፈቱ ራሳቸውንና ዘመዶቻቸው ሲያበለፅጉ ነገር ግን በሚያስተዳድሩት ክልልም ሳየቀር ለሚፈፅመው ግድያ፣ አፈና ህገወጥ ንግድ ኮንትሮባድ ህወሓት ሲወነጀልላቸው፤ በሚያስተዳድሩት ክልል ግብር ከፍሎ ሻይ ቤት የከፈተን የትግራይ ተወላጅ ንብረታቸውን እንደዘረፈ አገሩ ድንጋይ እንደሆነ መናጢ ድሃ ከሰው በታች እንደሆነ እያስተማሩ ሙሉ ሃጢያት የሚሸከም ድርጅትና ህዝብ (ህውሓትና ትግራዋይ) ሲያገኙ ለምን መታደስ ያስፈልጋቸውል፡፡ "የሃጥያታቸው ምንጭ ህወሓት ነው ጠላታቸው ወያኔና ትግራይ ናቸው" ቢናወጡ፣ በአመፁ ላይ የሚሳተፈው ይህንን ነው እያለ ያው ስለዚህ እነሱ ጋ ምንም ሃጢያት ካልተሰራ ምንም ቢሰሩ ሃጢያቱ የማይነካቸው ከሆነ ለምን መታደስ ያስፈልጋቸዋል፡፡ የሚሻለው አማራጭ አይተ በባላ እደሚባለው ዳዋውን ለዳዋው ህወሓትና ትግራዋይ ትተው በስመ ጥቅል ተሃድሶ ማሾፍ፣ ተሰብስቦ መበተን ከበቂ በላይ ስለሆነ ብዙ እንዲለወጡ ባንጠብቅ ጥሩ ይመስለኛል፡፡

በተለይ በተለይ የሚገርመው የትግራይ ተወላጅ ኦሮሚያ ሄዶ የኦነግን ቋንቋ ተምሮ (ኦሮመኛን አይደለም-ኦሮሚኛ መማርማ ብልህት ነው) የኦነግ ፖለቲካዊ ቋንቋውን ለማለት ፈልጌ ነው ተምሮ ገብቶት ኦነግ ሆኖ የኦሮሚያ ወጣቶችን በኦረሚኛ ቋንቋ ስለኦነግ ለመቀስቀስ ባንዲራ ይዞ ተገኘ ተብሎ ታሰረ ስሰማ፣ የት ሄጄ ልፈንዳ እንዳለችዋ ነው የሆነብኝ፡፡

ይህ ሰሞኑን እየሰማነው ያለነው ከዚህ ብሄር የመጣ ሊያበጣብጠንሲል ተያዘ የሚል የነ OBN እና የኦሮሚያ መንግስት ቃል አቀባይ ዘገባ ያልበሰለ ጨቅላ የፖለቲካ ጨዋታ ብቻ ሳይሆን አስቂኝ ድራምም ስለሆነ የደረስንበት እንደዋዛ እንደ ቀልድ እያሳሳቁ አገርን የማፍረስ ዘመቻው ተቀፅላ ስለሆነ በዚሁ ልውሰደውና ልተወው፡፡

ስለዚህ እያሳሳቁ አገር ለማፍረስ የተዘጋጁትን የኢህአዲግ ባስልጣናትን የፈለጉትን ያክል የሱባኤ ቀናት ቢቻል ዓመታት ቢሰጣቸው አላማቸው የዘረፉትን ዘርፈው አገር ማፍረስ ነውና ሊታረሙ ቀልባቸው አገርና ህዝብን ከጥፋት ለማዳን ይሰራሉ የሚል እምነት የለኝም፡፡

ኢህአዲግ በርግጥ መታረምና የሰው እልቂት መታደግ የሚፈልግ ከሆነ የፖለቲካ ውሳኔ፣ ቁርጠኝነት፣ ህግና ስርዓት ማስከበትን ተቀርጠው መጣል ያለባቸው ቱባ ጥጋበኛ ባለስልጣናቱን ቀርጦ የመጣል ከአገር ከብዙ ህዝብ ወይንም ከሰላማዊ ዜጎች የሚበልጥ ሙሰኛ ባለስልጣን እንደሌለ ሊያሳየን ይገባል፡፡

ኢህአዲግ እና አባል ድርጅቶቹ በእርግጥም መታደስ ይገባናል አንችላለንም ብለው የሚስቡ ናቸው? ጥሩ፤ በርግጥ የሚያስቡ ከሆነ ግልፅና ህዝብ በመንፈስም በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭትም በሚከታተልበት መንገድ ሁሉንም ችግሮች አፈረጥርጦ መነጋገር የሚያስችል መድረክ መፍጠርና በድብቅ ስለ ሂዎታችን በስመ ግምገማ የሚፈተፍተውን መስማት አለብን፡፡ ብዙ ዉሳኔዎቹ በቀጥታ በሂዎት የመኖርና ያለመኖር እጣፋነታችን ላይ ያነጣጠሩ የተጣመሙ አካሄዶች ከጊዜ ጊዜ እየበረከቱና እኛንም ስጋት ውስጥ እየከተቱን በመሆኑ ኢህአዴግ ስጋት ላይ እንድንኖር ካልፈለገ በስተቀር ስለኛ የሚዶለተውን ይሁን ለመፍትሄ ትጋት ሁሉ አስቀድመን የምንከታተልበት መድረክ ሊፈጥርልን ይገባል የሚል እምነት አለኝ፡፡

በነገራችን ላይ እጅግ አፁብ ድንቅ ከራሱ ይልቅ ለህዝብ (ለዜጎች) ቅድሚያ የሚሰጥ ገዥ በአለም ላይ አልተፈጠረም፡፡ ምክንያቱም አገር፣ ዜግነት፣ ዳርድንበር የሚሉት ተግባራትና ቃላት የገዥዎች እንጂ የተገዥዎች

ሆነው አያውቁምና፡፡ እንደኔ አንደኔ ዜጋ ተረጋግቶና በሰላም ዉሎ የማያድርበት አገር ባፍጢሙ ቢደፋ ግድ የለኝም ባይ ነኝ፡፡ የሶማሌ ህዝብ ሶማሊያን ጥሎ የተበተነው ሶማሊያ ሂወቱን የምትጠብቅ አገር ስላልሆነችለት ነው፣ የሶርያ፣ የኢራቅ፣ የሊብያ እና ሌሎች አገሮች ዜጎች ገዳያቸው እንኳን ማን እንደሆነ የማያውቁባቸው ስለሆኑ አገር ገደል ይግባ ብለው ጥለው እየተሰደዱ ነው፡፡

አገር አቅፌ ይዣዋለሁ፣ ዜጋ (ባሪያ፣አገልጋይ) የኔ ነው፣ ግብር ይከፍለኛል፣ የመንደር ጎረምሳ ሲያስቸግር ወታደር ይሆንልኛል፣ወዘተ ለምትለው ሰውን ያህል ታላቅ ፍጡር መጠበቅ ፤ሰላሙን እንዲያጣ ተፈጥሮአዊ ሞቱን እንዳይሞት ማለትም በእርጅና ወይን በበሽታ ከመሞቱ በፊት ቀድሜ ካልገደልኩት፣ መሞቱ የማይቀረውን ሰው ሲሞት፣ በእሳት ሲነድ፣ በጥይት ሲቀዘፍ ካላየሁ ብሎ ቆንጨራም፣ ድንጋይም፣ ክብሪትም፣ዲሞትፈርም ይሁን ሰንጢ ታጥቆ ሊላኛው እንደሱ አይነት ተገገር ምስኪን ካላጠፋሁ የሚለውን ወንጀለኛ ከማስታገስ፤ ካላጠፋሁ ከሚል የመንደር (የድንበር ውስጥ መንደር ነው) ጎረምሳን በህግና ስርዓት እንዲጠየቅ ከማድረግ ዳተኛ መሆን እራሱ ከተባባሪ ወንጅለኝነት ሊያድን የሚችል አይመስለኝም ፡፡ ጠግቦ ባደረ ጎረምሳ የመሞቻ ጊዜያችን እንዳይፋጠን በማገዝ ከታሪክም ከህሊናም ተጠያቂነት ራስን ማዳን ይገባል፡፡

በነገራችን ላይ በሂወት ብንቆይ ግብር በመክፈል ከጎረቤት ጋር ሲጣላ ወታደር በመሆን መሬት ሲራቆት አፈርና ውሃ እቀባ በማድረግ እንጠቅመወቀለን እንጅ መኖራችን አንጎዳውም፡፡ እየተገደልን ያለነው ሰዎች የምንጠይቀው የመሞቻ መንገድ መብታችን እንዲጠበቅልን ነው እንጂ ከመሞት እንዲያተረፈን አይደለም፡፡ ማትረፍ የሚቻል ቢሆን ግን ለማን ሰጥተው ለማን ሊከለክሉ እንደሚችሉ መገመት የሚያስቸግር አይመስለኝም፡፡

ከነዚህ ከማይታደሱት ሰዎች ልውጣና ወደ ሌላ ጉዳይ ልግባ፡፡ በአንድ ወቅት ለምንድነው ሁሉም እየዘለለ የትግራይ ህዝብና/ተጋሩ ላይ ፊጢጥ እያለ ካላጠፋኋቸው የሚለው የሚል ጥያቄ አንስቼ ለመልሱ በቀን በውን በሌሊት በህልና በቅዠት ስናውዝ አንድ በአገራችን አንቱ የተባሉ ፖለቲከኛ እኔ ያነሳሁትን አይነት ጥያቄ ተጠይቀው የመለሱት መልስ ስሰማ እንዲያውም እንዲህ አይነት ጥያቄ ባነሳ ማፈር መሸማቀቅ እንዳለብኝ ለራሴ ነግሬ በውንም በህልምም መልሱን መፈለግ እርግፍ አድርጌ ተውኩት፡፡

እኝህ እውቅ ፖለቲከኛ ያሉት ነገር ቢኖር የትግራይ ህዝብ እየተጠላ ያለው ሌላው ህዝብ ህወሓትን እየተቃወመ ለምን እኩል አብሮኝ አልተቃወመም ተብሎ ነው፡፡ የትግራይ ህዝብም እንደሌላው ሁሉ ፀረ ህውሓት መሆን ነበረበት በማለት ነው ብለውን እርፍ አሉ፡፡ እኔም መጠየቅ ስለምወድ......

1. ደርግን ሁሉም ኢትዮጲያ እኩል ታግሎታል? (በርግጥ መስዋእትነት አይበላለጥም አንድም ብዙ ነውና)
2. ከትግራይ ህዝብ ውጭ ያለው ለምን ህውሓትን መጥላት አስፈለገው?
3. እሺ መጥላትስ ከፈለገ ለምን ሁሉንም የኢህአዲግ አባል ድርጅቶች አልጠላም?
4. እኝህስ ፖለቲከኛ ከመናገራቸው በፊት ለምን ህውሓት ብቻ ተጠላ ብለው ለምን አልጠየቁም?
5. ሌሎች የመጥላትም የመውደድም መብት ካላቸው ለምን የመውደድም የመጥላትም መብት ለትግራይ ህዝብ ብቻ ተነጥሎ ተከለከለ ብለው አልጠየቁም?

መቸም ተምረው ተመራምረው እስከ አሜሪካ አገር ሄደው የ2ኛ ዲግሪ ሁላ ሰርዋልና እነዛን ያነሳኋቸውን ጥያቄዎች ጨምሮ ሌሎች ከኔ አቅም በላይ የሆኑትን ሳይቀር ማንሳት ነበረባቸው፡፡

እስኪ እኔ ለመመለስ ልሞክር፡-

1. ደርግን ሁሉም ኢትዮጵያዊ (ህዝብ) እኩል አልታገለውም ይህ እውነታ ነው ደርግን አምርሮ የታገለው በሰሜን አካባቢው በተለይ ደግሞ የትግራይ ህዝብ ነው ስለዚህ የኔን ያክል ደርግን አልታገላችሁትም እና አሁን ያሉት ፀረ ኢህአዴግ ነን ባዮች እንደሚደርጉት ቤታችሁን ካላቃጠልኩ፣ በድንጋይ ወግሬ ካገደልኳችሁ፣ መንገድ ዘግቼ ካላሰቃኋችሁ፣ ሞት ለእናት እያልኩ ካላሸማቀኳችሁ አላለም ቢል ትግሉ እጅግ አሳፋሪ አስነዋሪ ትግል ይሆን ነበር፡፡ ሌላው ቢቀር እኝህ ፖለቲከኛ የመጡበት ክልል ወጣቶች በማሰባቸው ምክንያት ብቻ ወይንም ኢህአፓ ይመስላሉ እየተባለ በነ ዓሊ ሙሳ ይገደል የነበረን ወጣት ከነበረው የመምሰልና የማሰብ መብትን ከመንፈግና ከመግደል ሂወት ገብሮ እሳቸውም ከመምሰልም ከማሰብም አልፈው ፓርቲ አቋቁሞመው እስከ መቃወም  እንዲደርሱ ታግሎ ሲያበቃ ሂሳብላወራረድ አላላቸውም፡፡
2. ከትግራይ ወጭ በተለይ በአማራና ኦሮሚያ ክልላዊ መንገስታት ያሉት ለምን ህወሓትን መጥላት አስፈለጋቸው ለምን ያላመማቸው ጋ ማከክ ፈለጉ በህወሓት የመማረር መብቱን ለምን ለትግራይ ህዝብ አይተውለትም እነሱ በሚያስተዳድራችው ብአዴንና ኢህዶድ ላይ ምሬታቸውን አይገልፁም (ምሬት ካላቸው) ምሬት ስላላቸውማ ከህወሓት ጋር ጨፍልቀው ወያኔ ትግሬ ይሙት ይጥፋ ስለሚሉት ቢከፋውም የግሉ ናቸው ለካ እያለ ይችለዋል፡፡ ስለዚህ ስለትግራይ ህዝብ ሲሆን ሲሆን ለቅሶው ራሱ ህዝቡ ያልቅስበት እናንተ የየክልላችሁን እምባ አብሱ፣ የየክልላችሁን አስተዳዳሪዎች እዛው በጠበላችሁ ያዙልን ማለት ነበረባቸው፡፡
3. ለምን ሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች አይጠሉም እነዚህ የጥላቻ ደቀ መዛሙርት እጅግ ዘረኞች ስለሆኑ አንድን አስተዳደር የሚያዮት ከየትኛው ብሄር፣ ብሄረሰብ ጎሳ፣ ወይንም ቤተሰብ እንደሆነ እንጅ የተሸለ ነው አይደለም ከሚል ፍትሄዊ መመዘኛ አይደለም፡፡

ስለዚህ ሲጠሉም ተግባርን አይተው ሳይሆን ትውልድ ሃረግ ብሄር ቆጥረው እንጂ የደረሰባቸወን አይተው አይደለም፡፡ በአማራ ክልል በቅማንት ህዝብ ላይ በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚተዳደርን ህዝብ በአማራ ክልላዊ መንግስት በሚታዘዝ ልዮ ሃይል ሲጨፈጭፎት ቃል መተንፈስ አቃታቸው፡፡ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በምዕራብ ሃረርጌ በክልሉ የሚኖሩ ቋንቋውን ባህሉን ማንነቱን የወረሱትን ሰዎች የዘር ሃረጋቸው ተፈጥሮ በጅምላ ሲገደሉ ገዳዮን ለማውገዝ ትንፍሽ አላሉም ይልቁንም የዚህ ብሄር ተወላጅ ወታደሮች ፈጁን ብለው በሺዎች ኪሎ ሜትር ርቆ ያለውን ህዝብ ወንጀለኛ ለማስመሰል ነበር የጣሩት፡፡

እኝህ ፖለቲከኛ ለምን እኔ/እና የጠላነውን የትግራይ ህዝብ አልጠላም ብለው ከመናገራቸው በፊት የተማሩት ትምህርት ተጠቅመው ከሻሼ (ቤቶች ድራማ ላይ ያለችው ሻሼ) በለጥ ባለደረጃ ከእውቀታቸው አንፃር ፈትሸው መናገር ይጠበቅባቸው ነበር መሰለኝ፡፡ ነገር ግን በኛ አገር የሚበቅሉት አንዳንድ እረ እንዳውም አባዛኞች ፖለቲካኛና ምሁር ነን የሚሉት ከተናገሩ በኋላ መስለኝ የሚያስቡት የመጣላቸው ነው የሚዘረግፉት የሃሳብ መቋጠሪያቸው ከጭንቅላታቸው ውጭ ስለሆነ ከዘረገፉት በኋላ ማሰብና መተንተኑን ጥቂት ለምናስበው ማሃይማን ስለሆነ የተወልን ልክ አሁን እኔ እደማደርገው አድረገን ያልተማርነው ሰዎች እደሰቅባቸዋለን እነሱም እየቆዮ እየቆዩ የምንስቅበትን ነገር ይጥሉልና፡፡ እኝህ ምሁር ፖለቲከኛ ከዚህ በፊትም አንድ ቃለ መጠይቅ ላይ መድሐኒአለም አካባቢ ያሉትን ፉቆች ብትቆጥር አብዛኛው የትግሬዎች ስለሆነ የህዝብ መማረር ትክክል ነው ብለው በፎቅኛ አስበው ሲናገሩ ሰምቻቸው ስለነበር ያው ናቸው ብየ እና ባልበሰለ ጭንቅላታቸው እንደሚያስቡ ስለገመትኩ ፈውስ ምህረቱን ለሳቸው አልኩኝ፡፡

እዚህ አገር የሚታደስም የሚማርም ፖለቲከኛ እና የፖለቲካ ፓርቲ ለማግኘት ብዙ ገና ብዙ መጓዝ ያለብን ይመስለኛል፡፡ ስለሆነም ኢህአዴግ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ተቃዋሚዎች እስኪሰለጥንና አዲስ ሆነው መወለድ ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ አሟሟታችን እንደያጥር ወይንም ከተፈጥሮአዊ ውጭ እንዳይሆን ሰማይ ደግፈን መኖር ግድ ሳይለን አይቀርም እላለሁ፡፡

## የህዝብ መድረኮች ለተሃደሶ የሚጠቅም ይሆን?

ኢህአዴግ በርግጥ ከልቡ ንስሃ መግባት የፈለገ ከሆን ነፃ የህዝብ መወያያ መድረኮችን (public dialogue forums) መፍጠር ያለበትና እነዚሁን መድረኮች በቀናነት መጠቀምም ያለበት ይመስለኛል፡፡ እነዚህ የህዝብ መድረኮች በቋሚነት የሚካሄዱና ሁሉም አይነት ጥያቄዎች ተነስተው ውይይት የሚደረግባቸው መሆን ቢችሉ እጅግ ጠቃሚ ናቸው የሚል እምነት አለኝ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት አሳታፊ መድረኮች የአገራችን ፖለቲካና የወደፊት እጣ ፋነታ፣ የህወሓት ይሁን የትግራይ የበላይነት እየተባሉ የሚሰበኩትም፣ ዜጎች በየክልሉ የሚያጋጥማቸው መንገላታትን፣ በአገልግሎት ሰጪ መስርያ ቤቶች ያለውን የመልካም አስተዳደር ችግርን፣ የስራ ፈጠራና የወጣቶቻችን፣ የትምህርት ስርኣታችን ወዘተ. እና ከዚህም ጠንከር ያሉ ሌሎች ጥያቄዎችና አስተያየቶችን ማስተናገድ የሚችል ከሁሉም የማህበረሰብ ክፍልና ብሄር ብሄረሰብ የተውጣጣ ሰፊ መሰረት ያለው የህዝብ መድረክ (inclusive public discussion platform) ቢኖረን የሚጠቅም ይመስለኛል፡፡